# የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚደረገው ውይይት

# የሚመራበት ሥርዓት እና ደንብ

ታኅሣሥ 2011 ዓ.ም

# <u>በተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚደረገው ውይይት የሚመራበት ሥርዓት እና ደንብ</u>

## 1. <u>መግቢያ</u>

በመላ አገራችን ሰላም እና መረጋጋት የሚፈጠርበትን ሁኔታ በጋራ ጥረት እና ተሳትፎ ለማረጋገጥ ሁሉንም ፓርቲዎች ያሳተፈ ውይይት ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

አገራዊ ምርጫ ነፃ ፍትሐዊና ተአማኒ እንዲሆን የሚያስችሉ የፖለቲካና የሕግ ለውጦች መከናወናቸውን ለማረጋገጥ፤ የዲሞክራሲ ተቋማትን በጋራ ለመገንባት እንዲቻል በፓርቲዎች መሃል ሊኖር የሚገባውን ትብብር ለማሳደግ፤

በፖለቲካ ፓርቲዎች መሀከል  አስፈላጊ ከሆነው ፉክክር ውጭ የሚታየውን ያለመተማመን በማስወገድ የጋራ ራዕይን ለመገንባት፤

በአገሪቱ እየተካሄደ ባለው ለውጥ (Reform) ምክንያት የተከሰቱ ችግሮች ላይ ተወያይቶ በጋራ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ሃሳቦችን በጋራ ለማዳበር በፓርቲዎች መካከል ውይይት ማካሄድ ጠቃሚ መሆኑ ስለታመነ፤

እስከአሁን በአገሪቱ ያለው የፖለቲካ ባሕል የሚሻሻልበት ሁኔታ ለማመቻቸት፤ በፓርቲዎች መካከል በጨዋነት እና በመከባበር ላይ የተመሠረቱ ውይይቶች በማድረግ ድርጅታዊ ትብብርን በመፍጠር የዲሞክራሲ አድማሱን ማስፋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች የክልል ምክር ቤቶች ውክልና በአንድ ፓርቲ የተያዘ በመሆኑ እና ሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሃሳባቸውን የሚገልፁበት መድረክ ስለሌለ በፖለቲካ ፓርቲዎቹ መሀከል ሊኖር የሚገባውን ውይይት በቀጣይነት የሚያስተናግድ መድረክ አስፈላጊነቱ ተቀባይነት ስላገኘ፤

ይህን የፖለቲካ ፓርቲዎች ውይይት የሚመራበትን ደንብ ማውጣት አስፈልጓል፡፡ ስለሆነም የፖለቲካ ፓርቲዎቹ በዚህ የውይይት ስርዓት እና ደንብ ለመገዛት ስምምነት አድርገዋል፡፡

## 2. ዓላማ

በፓርቲዎች መሀከል ሊኖር የሚገባውን ዲሞክራሲያዊ የሆነ ውይይት ዘለቄታዊ በሆነ መልክ ማካሄድ እና የፖለቲካዊ ልዩነቶችን ለማጥበብ ፍጹም ሰላማዊ የሆነ ውይይት መጠቀም፤

መሠረታዊ የሆኑትን የዲሞክራሲ፣ የሰብአዊ መብት እና የእኩልነት መርሆዎችን እንዲሁም የቡድን መብቶችን ማራመድ፤

በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን ሰላማዊ የሆነ ውይይት ውጤታማ ለማድረግ ልዩነቶች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ሁኔታዎች ሁሉ ማመቻቸት፤

በፓርቲዎች መካከል መተማመንን እና በትብብር መሥራትን ማበረታታት፤

አገራዊ እርቅ፣ አገራዊ መግባባትና አንድነት የሚጠናከርበትን ሁኔታ መፍጠር፤

የተለያዩ አመለካከቶችን እና እሴቶችን በመቻቻል ማስተናገድ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች የዲሞክራሲ ምሰሶዎች የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸትና አቅማቸውን መገንባት፡፡

## 3. ውይይቱ የሚመራበት መርሆች

ከዚህ በላይ በተ.ቁ 2 ላይ የተገለፀውን ዓላማ ለማሳካት የውይይቱ ተካፋይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መርሆች ማክበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

- በውይይቱ ሂደት ለአገራዊ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት፣
- መቻቻል፣
- መመካከር፣
- መደማመጥ፤
- መከባበር፤
- የሰጥቶ መቀበል መርህ፤

- በተሳታፊዎች እኩልነት ማመን
- የሌለውን ሀሳብ መረዳት እና ማክበር
- ምክንያታዊ መሆን፤
- ሀቀኝነት እና ጨዋነት ናቸው፡፡

## 4. ውይይቱ የሚካሄድበት ሥርዓት

ሀ) ፓርቲዎቹ በጽሑፍ ለምርጫ ቦርድ በዝርዝር ያቀረቡትን እና ለወደፊትም የሚያቀርቧቸውን አጀንዳዎች መሰረት በማድረግ ቦርዱ የሚያቋቁመው የባለሙያዎች የድጋፍ ኮሚቴ እና አወያዩ የአጀንዳዎቹን ቅደም ተከተሉን በማውጣት ለውይይት አቅርበው ያጸድቃሉ፡፡

ለ) የውይይቱ አጀንዳዎች ምን ምን መሆን እንዳለባቸው የሚወሰነው የመጀመሪያው ቀን የፓርቲዎቹ ስብሰባ ላይ ነው፡፡ ይሁን እና የመሰብሰቢያ ቦታ፣ ሰዓት እና ቀን እንዲሁም አወያዩን ከሰባት ቀን በፊት ለተወያይ ፓርቲዎች በምርጫ ቦርድ አማካይነት በደብዳቤ ይገለፃል፡፡

ሐ) ውይይቱ እንደ የአግባብነቱ የመረጃ ልውውጥ፣ የመክፈቻ ንግግር፣ የጥያቄና መልስ እንዲሁም የመዝግያ ንግግር ሊያካትት ይችላል፡፡

መ) በመወያያ አዳራሹ ውስጥ የተገኙ ተወያይ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው ምን ያህል ጊዜ ወስደው መናገር እንዳለባቸው አወያዩ ይወስናል፡፡

ሠ) በውይይቱ ወቅት ስምምነት ያልተደረሰባቸው ጭብጦች ሲኖሩ አወያዩ እነዚህን ጭብጦች ለይቶ አውጥቶ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

ረ) አወያዩ በእነዚህም ጉዳዮች ላይ የማስማሚያ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ በቀረበው ማስማሚያ ሀሳብ ላይ በዕለቱ ስምምነት ካልተደረሰ በዚህ ሰነድ ተራ ቁጥር 9(ሐ) እና 11(መ)መሠረት ታዛቢዎቹ በሚያቀርቡት የማስማሚያ ሀሳብ መሰረት ጉዳዩ አድሮ እንዲብላላ ማድረግ ይገባል፡፡

ሰ) ታዛቢዎቹ ሀሳብ የሚያቀርቡት ተወያዮቹ በውይይቱ ወቅት ስምምነት ላይ ሳይደርሱ ሲቀር ብቻ ነው፡፡ የሚሰጡትም ሀሳብ ያልተስማሙትን ወገኖች ሊያስማማ ሊያቀራርብ የሚችል ሀሳብ ሲኖራቸው እና ይህም ሀሳባቸው በአወያዩ እና በባለሙያ ድጋፍ ኮሚቴው ተቀባይነት ሲኖረው ብቻ ነው፡፡

ሸ) ከላይ 4 (ሠ እና ረ) ላይ በተገለጸው ጊዜ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ ለውይይቱ ምክንያት የሆነው ጭብጥ በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ እንዲያገኝ በማድረግ ጉዳዩ ይቋጫል፡፡

## 5. ከውይይቱ ተሳታፊዎች የሚጠበቀው ኃላፊነት

ሀ) የውይይቱ ተሳታፊዎች በዚህ ሰነድ ተራ ቁጥር 3 የተገለጹትን መርሆች መሰረት በማድረግ ሀሳባቸውን የሚያቀርቡት ግልጽ ገንቢ እና ጨዋነት በተሞላበት ሥነ ምግባር ነው፡፡

ለ) የውይይቱ ተሳታፊዎች የሚያቀርቡት ሀሳብ ከቀረበው አጀንዳ ጋር ብቻ የተያያዘ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡፡ በተሳታፊዎች ጸድቆ ውይይት እየተካሄደ ካለበት አጀንዳ ውጪ የራስን አጀንዳ የሚያንፀባርቅ የጣልቃ ገብነት ሁኔታ በፍጹም አይፈቀድም፡፡

ሐ) የሚሰጡትም አስተያየቶች በሌሎች ተሳታፊዎች ስብዕና ላይ ሊያነጣጥር በፍጹም አይገባም፡፡

መ) የውይይቱ ተሳታፊ ፓርቲዎች በተያዘው አጀንዳ ላይ አንዱ ከሌላው የሚለይበትን እንዲሁም የሚስማማበትን ለይተው መግለጽ ይገባቸዋል፡፡

ሠ) የውይይቱ ተሳታፊ የሆነ ወገን ውይይቶቹ በሚከናወኑበት ወቅት በዚህ ስርዓት እና ደንብ ላይ የተገለጹትን ሁኔታዎች ጥሶ መገኘቱን አወያዩ ሲገነዘቡ ይህንን ሁኔታ ለተወያዮቹ በግልጽ በማሳየት የውይይቱ አካሄድ ላይ እንቅፋት ሆኖ በተገኘው ተወያይ ላይ ለተፈፀመው ጥፋት ኃላፊ ይሆን ዘንድ ውሳኔ ያሰጣሉ፡፡

ረ) ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 5(ሠ) በተገለጸው መሠረት ጥፋት የፈፀመውን ተወያይ ከጥፋቱ እንዲታረም በተሳታፊዎች ይመከራል፡፡

ሰ) ከዚህ በላይ የተገለፀውን ምክር ያልሰማ ተወያይ እንዲሁም ጥፋቱ ተደጋጋሚ ሆኖ ውይይቱን ለማስኬድ አስቸጋሪ ሁኔታ ከፈጠረ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ጉባኤው ያደርጋል፡፡

## 6. አወያይ

ሀ) በአወያይነት የሚሰየመው ሰው በአብዛኛው ፓርቲዎች ተቀባይነት ያለው እና ገለልተኛነቱ የተረጋገጠ ሊሆን ይገባል፡፡

ለ) ተወያይ ፓርቲዎች አወያይ ሊሆኑ ይገባል ያሏቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ለቦርዱ በጽሑፍ ያቀርባሉ፡፡

ሐ) ተወያዮች በሚያቀርቡአቸው የአወያዮቹ ዝርዝር ላይ ሀሳብ እንዲሰጡ ተደርጎ መድረኩ የተቀበላቸውን አወያዮች ቦርዱ መዝግቦ ይይዛል፤ እንደ የአስፈላጊነታቸው በየውይይቱ መድረክ ይመደባሉ፡፡

## 7. የአወያይ ኃላፊነት እና ግዴታ

ሀ) አወያዩ የዕለቱን አጀንዳ ያስታውቃል፤ መድረኩን ይመራል፤ ተወያዮቹ የተሰጣቸውን ጊዜ በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡

ለ) ውይይቶቹ በቀረበው አጀንዳ ላይ በተነሱ ነጥቦች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

ሐ) ተወያይ ፓርቲዎች እኩል የመወያያ ጊዜ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

መ) አወያዩ በወቅቱ ያሉትን ተወያዮች በማማከር ይህን ስርዓት እና ደንብ በሚተላለፍ ተወያይ ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

ሠ) የውይይቱን ሂደት በየጊዜው በአግባቡ በኦዲዮ፣ በቪዲዮ እና በጽሑፍ የተመዘገበ (documented) መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

## 8. ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች ኮሚቴ

ሀ) በተፎካካሪ ፓርቲዎች መሀከል የሚደረጉትን ተከታታይ ውይይቶች የሚያግዝ ለምርጫ ቦርዱ ድጋፍ የሚሰጥ ከሁሉም የሙያ መስክ (Inter disciplinary) የተውጣጡ ገለልተኛ የሆነ የባለሙያ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

ለ) የድጋፍ ሰጪ ኮሚቴው በውይይቱ ላይ ተሳታፊ በሆኑት ፖለቲካ ፓርቲዎች መሀከል ልዩነት እየሰፋ ከሄደ ይህንኑ ልዩነት ለማጥበብ የሚረዱ ሀሳቦችን በአወያዩ በኩል ለመድረኩ ያቀርባሉ፡፡

ሐ) የውይይት መድረኩ በሚያስቀምጠው አቅጣጫ (guidance) መሠረት የመነሻ ሀሳቦች እና የመወያያ ሰነዶችን አዘጋጅቶ በአወያዩ በኩል ያቀርባል፡፡

መ) በውይይቱ ሂደት ላይ ለአወያዩ የሙያ እገዛ ያደርጋል፡፡

ሠ) የውይይቱን ሂደት በየጊዜው በአግባቡ በኦዲዮ፣ በቪዲዮ እና በጽሑፍ የተመዘገበ (documented) መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ተወያይ ፓርቲዎችም ሲጠይቁ ትክክለኛ ቅጂው ይሰጣቸዋል፡፡

ረ) የውይይቱ መድረክ ከመጀመሩ በፊት ቀደም ሲል የተደረጉ ውይይቶችን በአጭሩ በመግለጽ ጉባኤው ያለፈውን ውይይት እንዲያስታውስ ያደርጋል፡፡

ሰ) መድረኩ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ውይይቱ የደረሰበትን ሁኔታ የሚያስረዳ ጋዜጣዊ መግለጫ (Press Statement) ይሰጣል፣ ያሰራጫል እንደ አግባብነቱ ፕሬስ ኮንፈረንስ ያደራጃል፡፡

## 9. ታዛቢዎች

ሀ) በውይይቱ መድረኩ የሚመረጡ ያለፈውን ትውልድ እና የአሁኑን ትውልድ ድልድይ ሆነው ሊያገናኙ የሚችሉ ገለልተኛ የሆኑ ከቀረበው ጉዳይ ጋር የተዛመደ እውቀት ያላቸው ስመ ጥር የሆኑ ግለሰቦች በታዛቢነት ይገኛሉ፡፡

ለ) የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማህበር፣ የደራሲያን ማህበር፣ የሳይንስ አካዳሚ፣ የሴቶች የሕግ ባለሙያዎች ማህበር፣ የመምህራን፣ የሰራተኞች፣ የአሰሪዎች ማህበራት ወኪሎች እንዲሁም የውይይት መድረኩ በየጊዜው እንደ የአስፈላጊነቱ የሚጨምራቸው የሲቪል ማህበራት፣ ወጣቶች እና የሌሎች የህብረተሰብ ወኪሎች በታዛቢነት ይወከላሉ፡፡

ሐ) የውይይቱ ተሳታፊዎች በቀረበው አጀንዳ ላይ መስማማት ሲያቅታቸው ታዛቢዎች የማስማሚያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ በአወያዩ እና በድጋፍ ሰጪው ኮሚቴ አማካኝነት ሊጠየቁ ይገባል፡፡

## 10. <u>የመገናኛ ብዙሀን ሚና</u>

ሀ) ውይይቱ ከመጀመሩ በፊት በእለቱ በቀረበው አጀንዳ ላይ ጉባኤው ለመገናኛ ብዙሃን ስብሰባው ክፍት የመሆኑን እና  የአለመሆኑን ጉዳይ በአብላጫ ድምፅ ይወስናል፡፡ በተጨማሪም ተወያዮቹ ለመገናኛ ብዙሃን ሊሰጡ ስለሚችሉት መግለጫ ጉባኤው በአብላጫ ድምፅ ይወስናል፡፡

ለ) ጉባኤው የደረሰበትን ደረጃ በየጊዜው የሚያስረዳ ጋዜጣዊ መግለጫ (Press Statement) በድጋፍ ሰጪ ባለሙያ አማካኝነት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

ሐ) የውይይት መድረኩ ጉልህ የሆነ ልዩነት ሲኖር ወይም ጉልህ ስምምነት ላይ ሲደርስ መድረኩ በሚወስነው መሰረት ሁሉን አቀፍ የፕሬስ ኮንፍረንስ ይጠራል፡፡

## 11. <u>ስምምነት ያልተደረሰባቸውን ጭብጦች</u>

ሀ) የውይይቱ ተሳታፊ ፓርቲዎች በቀረቡት ጭብጦች ላይ በተቻለ መጠን በጋራ መግባባት/Consensus/ ውሳኔዎች ይሰጣሉ፡፡

ለ) በውይይቱ ወቅት በተወያይ ፓርቲዎች መኸከል ስምምነት ያልተደረሰባቸው ጭብጦች ሲኖሩ አወያዩ የሚያቀራርብ ወይም ለስምምነት የሚያበቃ ሃሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡

ሐ) አወያዩ የተወያዮችን ሃሣብ መሠረት አድርጎ ባቀረበው ሀሳብ መስማማት ካልተቻለ፤ ወይም አስማሚ ሀሳብ ማቅረብ ሳይችል ሲቀር፤ አወያዩ ጉባዔውን አማክሮ ንዑስ ኮሚቴ ከተወያዮቹ መሀል በማቋቋም አማራጭ ሀሳብ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

መ) በቀረበው አማራጭ መሰረት ስምምነት ላይ ካልተደረሰ፤ ስምምነቱ ላይ ያልደረሱ ተወያዮች ብቻ በጉዳዩ ላይ ድርድር የሚያካሂዱበት መድረክ ይመቻቻል፡፡ በዚህም መድረክ በሚደረግ ውይይት ስምምነት ላይ ካልተደረሰ ይህንኑ መዝግቦ ወደ ሚቀጥለው አጀንዳ ውይይቱ ይሸጋገራል፡፡

## 12. <u>የመወያያ ቋንቋ</u>

ውይይቱ/ድርድሩ የሚካሄደው አሁን የሥራ ቋንቋ ነው ተብሎ በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው ቋንቋ በአማርኛ ነው፡፡ ይሁን እና ይህን ቋንቋ ለማይናገሩ ተወያዮች የውይይቱ/የድርድሩ ተሳታፊ መሆን ይችሉ ዘንድ ቦርዱ አስተርጓሚ ያቀርባል፡፡

## 13. <u>ያልተሸፈኑ ጉዳዮች</u>

በዚህ ስርዓት እና ደንብ በግልጽ ያልተሸፈኑ ሁኔታዎች ተሳታፊ ወገኖች፣ አወያዮች፣ የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች እንዲሁም ታዛቢዎች የሚያቀርቧቸውን ሀሳቦች መሰረት በማድረግ በወቅቱ ለተከሰተው ጉዳይ መፍትሔ መስጠት ይገባል፡፡

## 14. <u>ማሻሻያ</u>

ይህ ሥርዓት እና ደንብ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ በተዋዋዮቹ ጠያቂነት በውይይቱ/በድርድሩ ተሳታፊዎች አብላጫ ድምፅ ውሳኔ መሰረት የሚሻሻል ይሆናል፡፡

## 15. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ ሥርዓትና ደንብ በውይይቱ/በድርድሩ ተሣታፊ ፓርቲዎች በአወያዮች፣ በታዛቢዎች እና በድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች ኮሚቴ ቡድን ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## 16. የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ስርዓት እና ደንብ በዚህ ደንብ ላይ ለመወያየት ፍቃዳቸውን በገለጹ ስማቸው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት እና ወደፊት በፈቃዳቸው በዚህ ሰነድ ላይ ስምምነታቸውን በሚገልፁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ሰነዱ ከጸደቀበት ከዛሬ ጥር 2 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ መድረክ ውይይቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ የፀና ይሆናል፡፡

## 17. ደንቡን ያፀደቁት የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

| ተ.ቁ | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

| ተ.ቁ | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

| ተ.ቁ | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

| ተ.ቁ | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

| ተ.ቁ | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

| ተ.ቁ | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

| ተ.ቁ | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

| ተ.ቁ | የፓርቲው ስም | የፓርቲው ተወካይ | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |